# የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው ሕዝብ —ሠራተኛ፣ገበሬ፣ነጋዴ፣ወታደር፣ምሁር— መብትና ጥቅም የሚታገል ጋዜጣ

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ይቀደም::

ቁጥር 22 ቀን 4/6/67


## የኤርትራን ችግር እንዴት በትክክል ለመፍታት ይቻላል?

'አንድ የተጨቆነ ብሄር/ነሽን/ ህይወቱን እንዴት እንደሚያደራጅና የወደፊት ተቋሙን መልክ እንደሚይዝ የሚወስኑት የኢኮኖሚ የፖለቲካና የባህሉ ሁኔታዎች ናቸው::እያንዳንዱ ብሄር የራሱ የሆነ መፍትሄ ሊኖረው ይችላል::ዲያሌክቲካዊ አቀራረብ የሚያስፈልገው ነገር ቢኖር በቅድሚያ የብሄሮች ጥያቄ ነው::'

'ለመድገም:ከተጨባጭ ታሪካዊ ሁኔታዎች መጀመር:ትክክለኛ ዲያሌክቲካዊ የሆነ አቀራረብ — የብሄሮችን ጥያቄ ለመፍታት ቁልፉ ይህ ነው::' ጄ. ስታሊን:ማርክሲዝም ኤንድ ዘ ናሽናል ኩዌስቸን

'የብሄሮች ጉዳይ በከበርቴ ህብረተሰብ ውስጥ ታሪካዊ ቦታ አለው::ይህን በመመልከት የብሄራዊ ንቅናቄዎችን ታሪካዊ ስፍራ ማርኮሲስት የሆነ ሁሉ ሙሉ በሙሉ ያጎቅላቸዋል/ይደግፋቸዋል/::ለጠባብ ብሄረኛነት ምክንያት እንዳይሆንና የቡርዡዋ አይዲዮሎጂ ጋዜደራዊ ንቃትን እንዳይጋርድ ግን ይህ ድጋፍ በንቅናቄዎቹ ውስጥ ላለው ተራማጅ ክፍል ብቻ መወሰን ይኖርበታል::' ሌኒን:ኮ.ዎ.ቮ20: ገጽ 34

የኤርትራ ሕዝቦች የሃይለስላሴን ፋሽስታዊ አገዛዝ መቋቋም ከጀመሩ ይኸው አስራ ሶስት አመታት አለፈዋል::በነዚህ አመታት ውስጥ በነዚህ ሕዝቦች ላይ የደረሰው ግፍና በደል ተቆጥሮ የማያልቅ ነው::አሁን እነዚህ መስመሮች በሚፃፉበትም ወቅት በኤርትራ ውስጥ፣ በዋናው ከተማ፣ በነፃ አውጭ ግንባሮችና በኢትዮጵያ ሰራዊት መካከል ውጊያ እየተካሄደ ነው:: ይህም ሲሆን በብዙ ሰላማዊ ሕዝብ ላይ የህይወትና የንብረት ጥፋት ይደርሳል፣ የስንቱ ንፁህ ደም በከንቱ ይፈስሳል::የሃይለስላሴ መንግስት ከወደቀ ወዲህ በሰላም በቀላሉ ሊፈታ ይችል የነበረው የኤርትራ ጥያቄ ባሁኑ ጊዜ ወደከፍተኛ የወንድማማች ደም መፋሰስና እልቂት ደርሶ አለ::ይህ ሁኔታ ከቀጠለ የኤርትራ ሕዝቦችና የኢትዮጵያ ሕዝቦች ፈጽመው አብረው ለመኖር ከማይችሉበት፣ ፍፁም መቀራረብ ከማይቀርበት እስጊ ሁኔታ ላይ እንደሚደረስ ምንም ጥርጥር የለውም::ከዚህ ከሚያቆራርጥ ሁኔታ ላይ እንዳይደረስ ከተፈለገ በጣም አስቸኳይ በሆነ መንገድ ይህ የርስበርስ መፋጀት ቆሞ ሰላማዊ መፍትሄ መገኘት አለበት::በሁለቱም ወገኖች በኩል ለሰፊው ሕዝብ —ለኤርትራና ለኢትዮጵያ ሕዝቦች— ደህንነትና የወደፊት ግስጋሴ የሚያስቡ ካሉ ይህ ሰላማዊ መፍትሄ ሊገኝ ይችላል::

ይሁንናም ይህ መፍትሄ እንዴት ሊገኝ እንደሚችል ከማሰላሰላችን በፊት የኤርትራን ታሪክ ባጭሩ መመልከትና ሁኔታውም ከዚህ እንዴት እንደደረሰ ማጥናት አለብን::እንዲሁም ባሁኑ ጊዜ በቀይ ባህር አካባቢና ኢትዮጵያንም በሚመለከተው በኩል በአለም አቀፍ ደረጃ ጊዜያዊው የሃይሎች አሰላለፍ እንዴት እንደሆነ ማጤን አለብን::እነዚህን ካላደረግን ትክክለኛውንና ተጨባጩን ሁኔታ ለማየትና ለማሳየት ካለመቻላችንም በላይ በዚህም ሆነ በዚያ በኩል የሚኖረን አቀራረብ ስህተተኛ ሊሆን ይችላል::

### 1. የኤርትራ አጭር ታሪክና የራስን እድል በራስ ስለመወሰን መብት

የኤርትራን ትግል በሚመለከተው በኩል እስከዛሬ ድረስ የወጡት የግንባሮቹ ጽሁፎች ሊያሳምኑን የሚፈልጉት አንድ ነገር አለ::ይኸውም፣ ዛሬ ኤርትራ ተብሎ የሚጠራው አገር፣ ይህ የጣሊያን ቅኝ ገዥዎች ባለፈው ክፍለዘመን መጨረሻ ላይ ይህንን ስም ያወጡለት የሰሜን ምስራቅ ክፍል በጥንቱም ጊዜ ቢሆን የአበሻ መንግስት ወይም የአገር ክፍል እንዳልነበረ ነው:: እኤአ በ1967–68 ግድም ይወጡ የነበሩት አንዳንድ ጽሁፎችማ ከነጭራሹ የቋንቋም፣የባህልም፣

የሃይማኖትም ግንኙነት በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል አልነበረም እስከማለት የደረሱበት ወቅት ነበር::ከዚያ ወዲህ ታትሞ የተሰራጨ:'ኤርትራ:— ታሪክ:ጂኦግራፊ:ኢኮኖሚ' የሚል:ቀን ያልተፃፈበት አንድ የግንባሩ ጽሁፍ 'እንደእውነቱ ከሆነ መቼውንም ቢሆን ኤርትራ የኢትዮጵያ ክፍል ሆና አታውቅም'ካለ በኋላ:በዘር:በቋንቋዎች:በሃይማኖቶች:በጂኦግራፊ ሁለቱ አገሮች ምን ያህል ልዩ እንደሆኑ ለማስረዳት ይሞክራል::እርግጥ ነው፣ 'ኢትዮጵያ' የሚለውን ቃል እንደምኒልክ የንጉስነገስት መንግስት ግዛት ብቻ ከወሰድነውና ከምኒልክ በፊትም ሆነ ከፌዴሬሽኑ ወዲህ ያለውን ሁኔታ ወደጉን ከተውን ይህ አባባል —ማለትም:የኢትዮጵያ ክፍል አልነበረችም የሚለው— ያስኬዳል::ይሁንናም:የተባለው ጽሁፍ እራሱ አለፍ አለፍ ለማመን እንደተገደደው ሁሉ ዛሬ ኤርትራ ከተባለችው አገር ዋናው ክፍል የጥንቱ የአበሻ መንግስት አካል እንደነበር ምንም ጥርጥር የለውም::በተረፈ:የዘር:የቋንቋ:የሃይማኖት 'አለመመሳሰል' የሚለው በእውነቱ ምንም ክርክር የሚያስፈልገው ስላልሆነ ወደጉን እንተወዋለን::

ኤርትራ የተባለው የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ክፍለአገር ያሁኑን ስሙን ያገኘው በ1889 የጣሊያን ቅኝ ሆና በጣልያን መንግስትና በምኒልክ መካከል የውጫሌ ውል በተፈረመበት ጊዜ ነበር::ከዚህ በላይ ያነሳነው የኤርትራ ግንባር ጽሁፍ የሚጠቃቀሰው የተረቫስኪስ የኤርትራ ታሪክ መጽሃፍ 'ከዚያ በፊት —ማለት ከ1889 በፊት— ኤርትራ ምንም አንድነት:አንዳችም የራስዋ መንግስት:የራስዋ ስም እንኳን አልነበራትም'ይላል::<u>በኤርትራነት</u> ከታሰበ ይህም ትክክል ነው::ከውጫሌ ውል በፊት ኤርትራ የሚባል አገር አልነበረም::እንግዲህ የጥንቱስ?

ለስድስት ወይንም ሰባት ክፍለዘመናት በዚህ በአፍሪካ ክፍል አሸብርቆ የነበረው የአክሱም ስልጣኔ ዛሬ ኤርትራ የተባለውንም አገር ያጠቃልል እንደነበር ብዙ የሚያከራክር አይደለም::የግንባሩ ፀሃፊዎች እራሳቸው 'ኤርትራ የአክሱም ስልጣኔ እምብርት ነበረች' ብለው የፃፉበት ወቅት ነበር::ደግሞም አክሱማውያን ከመውደቂያቸው በፊት ቀይ ባህርንም ተሻግረው ደቡብ አረብን ለጥቂት ጊዜም ቢሆን አስገብረው እንደነበር የታወቀ ነው::የታሪክ ፀሃፊዎች እንደሚገምቱት ከሆነ፣ አሁን የኤርትራን ዋና ክፍልና ከመረብ አገር ያለውንም አገር የያዙት የትግራይ ነገዶች የተፈጠሩት:አገዎች የአክሱምን ስልጣኔ ደምስሰው አክሱማውያንን ከከላለሉ በኋላ፣ ከዘጠነኛው እስከአስራሁለተኛው ክፍለዘመን ግድም በነበረው ጊዜ ውስጥ ነበር::ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከጣልያን ቅኝ አገዛዝ መምጣት ድረስ፣ የኤርትራ ዋና ክፍሎች የሆኑት ሃማሴን:አከለጉዛይና ሰራዬ፣ አንዳንዴ ጥብቅ በሆነ አንዳንዴም በላላ መልክ፣ አክሱምን በተካው በአበሻ መንግስት ስር እንደነበሩ ታሪክ ይመሰክራል::በዚሁ በአበሻ መንግስት ስር የሆነው ገዥያቸውም 'ባህረነጋሽ'ይባል እንደነበር ተደጋግሞ ተገልጿል::

ይሁንናም፣ በ1557 ቱርኮች ምጽዋን ይዘው በዙሪያው ያለውን ቆላ አገር የሃርቂቆ ነይብ በሚባለው የቤጃ ባላባቶች ዘር ስር ያስተዳድሩት ነበር::ይህ ሁኔታ ለሶስት መቶ አመታት ቀጥሎ በ1872 ግብጾች ምጽዋን ያዙ::በሌላ በኩልም ግብጾች በ1875 ሀረርን ይዘው እንደነበር ይታወሳል::በዚሁ አመት:የኤርትራን ደጋ አገር:ከላይ የተጠቀሱትን ክፍሎች ለመያዝ ሲሞክሩ በጉንደት ላይ በአጼ ዮሃንስ ሰራዊት ተሸንፈው ወደምጽዋ ተወርውረዋል::በሚቀጥለው አመት:በ1876:እንደገና ሙከራ ሲያደርጉ በጉራ ላይ ከበፊቱ በባሰ ሁኔታ ተሸንፈዋል::

አጼ ዮሃንስ ምጽዋንና ከበስተኋላው ያለውን:ያኔ ቦጐስ ተብሎ ይታወቅ የነበረውን: አገር በእንግሊዞች አማካይነት ወደራሱ ግዛት ለመመለስ ሞክሮአል::በሰኔ 3 ቀን 1884 በንግሊዝ:በግብጽና በአጼ ዮሃንስ መካከል በተፈረመው ውል መሰረት ግብጾች ሰራዊታቸውን ከዚያ ሰፈር ሲያስወጡ:የተባሉት ክፍሎች ወደኢትዮጵያ ይመለሳሉ ተብሎ ነበር::ነገር ግን የእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም ዮሃንስን በማታለል:በ1885 ጣሊያኖች ምጽዋን ይዘው በግብጾች ቦታ እንዲተኩ አደረጋቸው::የጣሊያን ቅኝ አገዛዝ ወዲያውኑ ደጋውን ኤርትራ ለመያዝ ሙከራ ማድረግ ጀመረ::ይሁንናም በ1886 እና87 በተከነይቴና በዶጋሌ:በራስ አሉላ መሪነት የዐ

ሃንስ ሰራዊት ጣሊያንንም አራውጦ እንደገና ወደባህሩ መለሰታል::በ1889 አገርወዳጁና የዋሁ ዮሃንስ ከደርቡሾች ጋር ሲዋጋ በመተማ ሲሞት:ጊዜውን ሲጠብቅ የነበረው የሸዋው ንጉስ ምኒልክ 'የኢትዮጵያ ንጉስ ነገስት' ተብሎ ዘውድ ጫነ::ወዲያውኑም:ከጥንትም ጀምር ውጭ ውስጡንም ሆነ በይፋ ይደገፋትና መሳሪያ ያቀበሉት ከነበሩት የጣሊያን ቅኝ ገዥዎች ጋር የውጫሌን ውል ተፈራረመ::ዮሃንስ ሲሞት ጊዜ ለፍቶበት የነበረውንም ከመረብ ወዲያ ያለውን አገር ለጣሊያኖች ሸጠ::

ምንም እንኳን በ1896 የአድዋ ጦርነት ተደርጉ የጣሊያን ቅኝ አገዛዝ ቢደመሰስና የውጫሌም ውል ቢሰረዝ:ኤርትራን በማስለቀቅ ፈንታ ምኒልክ የጣሊያን ቅኝ አገዛዝ እንዳለ እንዲቆይ ሌላ ውል ተፈራርሞአል::አንዳንድ ፀሃፊዎች እንደሚሉት:ምኒልክ ይህንን ያደረገበት ምክንያት:በዚያን ጊዜ በሰሜን ኢትዮጵያ የነበረው ታላቅ ረሃብ ጣሊያኖችን ወደባህሩ እንዳይወረውራቸው ስላገደው ነው::ሌሎችም ምክንያቶች ይሰጣሉ::ለማንኛውም የትግራይ ሕዝቦች አንድ ላይ እንዳይሆኑ:እንዲከፋፈሉ በመፈለጉ ነው ይላሉ::ወጣም ወረደ:የዛሬይቱ ኤርትራ የተፈጠረችው በዚህ ሁኔታ ነበር::

ጣሊያኖች ለግማሽ ክፍለዘመን ኤርትራን ከበዘበዙና ሕዝቡን ከጨቆኑ በኋላ:እንደሚታወቀው:በ1941 ካገሪትዋ እንዲባረሩ ተደረገ::ኤርትራ በእንግሊዝ ተጠባባቂነት ስር ለአስር አመታት እንድትቆይ ስትደረግ በነዚህ አመታት ውስጥ በመጠኑም ቢሆን ዲሞክራሲያዊ ኑሮን ለማየት በቅታለች::ነፃ ጋዜጦች:የወዛአደር ማህበራት:የፖለቲካ ፓርቲዎች ነበሩዋት::

በ1952 ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን መልክ ስትያያዝ:የሃይለስላሴ መንግስት ሳይውል ሳያድር የፌዴሬሽኑን ህጎች መጣስ ጀመረ::አገሪትዋ በ1962 በጠቅላይ ግዛትነት በጉልበት እስከተያዘችበት ወቅት ድረስ:የኢትዮጵያ መንግስት የኤርትራን ነፃና ዲሞክራሲያዊ ድርጅቶች በተንኮልና በጉልበት ደምስሶአቸዋል::ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን የመያያዝ ነገር መጀመሪያውንም የኤርትራ ሕዝብ ያልተጠየቀበትና ያልተስማማበት በተባበሩት መንግስታት:በተለይም በዚያን ጊዜ በዚህ ድርጅት ውስጥ ፈላጭ ቆራጭ በነበረው የአሜሪካን መንግስት ትእዛዝ ነበር::ከላይ የተገለፀው ጠቅላላ ሁኔታ ከአስር አመታት በኋላ ወደነፃነት ግንባር መፈጠርና ከዚያም ወደ 13 አመታት የመሳሪያ ትግል መርቶአል::

እንግዲህ ጠባጡ የኤርትራ ታሪክ ይህ ሲሆን:የኤርትራ ነፃ አውጭ ግንባሮች ጸሁፎች በየጊዜው ይህንን ታሪክ በሌላ መልክ ለማቅረብ ሞክረዋል::ይሁን እንጂ:ይህንን እንዲያደርጉ የሚያስገድዳቸው አንዳችም ነገር አልነበረም፣ የለምም::ለአንድ ሕዝብ የራሱ ማንነት /አይደንቲቲ/ በግልጽ ከታየው በማንኛውም ጊዜ የራሱን እድል ከመወሰን ማንም ሊገታው አይችልም::ከሌሎች ሕዝቦች ወይም ብሄሮች ጋር በታሪክ መያያዙ:በመሰረቱ የራሱን እድል በራሱ የመወሰንና ከፈለገም የመገንጠል መብቱን አያስቀርበትም::

ኤርትራ በርካታ ያሉ ብሄሮችን/ናሽናሊቲስ/ የያዘች ቢሆንም የሃምሳ አመት ቅኝ አገዛዝና በተለይም የአስር አመቱ የፖለቲካ ኑሮ በመጠኑም ቢሆን ለኤርትራ ሕዝቦች አንዳች አይነት ማንነትን እንደሰጣቸው ለመገመት ይቻል ይሆናል::ኤርትራውያን ይህንን ማንነት በጣቂ አስራ ስስት አመታት ሙሉ የራሳቸውን እድል የመወሰን መብታቸው እንዲታወቅላቸው ቢታገሉ ቆይተዋል::የሃይለስላሴ መንግስትም ሆነ ጊዜያዊው የወታደር መንግስት የኤርትራን የነፃነት ግንባሮች 'ጥቂት ወንበዴዎች':'ሸፍቶች' ወዘተ. ማለታቸው ይህንን ሃቅ በምንም መንገድ አይለውጠውም::የኤርትራ የነፃነት ተዋጊዎች እንደዚያ እንደሚባሉት ቢሆኑ ኖሮ የኤርትራ ሰፊ ሕዝብ እነርሱን በማቀፍ ፈንታ አሳልፎ በሰጣቸው፣ እራሱ በያዛቸውና ባጠፋቸው ነበር::ስለኤርትራ የወደፊት እድል ከግንባሮቹ ጋር ለመነጋገር በመጀመሪያ ለግንባሮቹ የረጅም ጊዜ የነፃነት ትግልና ለተዋጊዎቹ ትክክለኛ የታሪክ ስፍራቸውን መስጠት ያስፈልጋል::ይህን መጣቱ አይበዙምና::

የኤርትራ ሕዝቦች ትግል -የሃይለስላሴን መንግስት ካከሰሩትና ከጣሉት ዋና ነገሮች አንዱ መሆኑ አይታወቅ፣ በአሁኑ ጊዜ የነዚህን ሕዝቦች የራሳቸውን እድል የመወሰን መብት አለማወቅና አሁን ደርጉ እንደሚያደርገው የጉልበት መፍትሄ መፈለግ በኤርትራ ሕዝቦች ላይ ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ ሕዝቦችም ላይ ታላቅ ጉዳትን ማድረስ ነው:: ወታደራዊው መንግስት በዚህ ጥያቄ ላይ ፈጽሞ የሃይለስላሴን መንግስት ጉዳና መከተል የለበትም:: ጊዜው የሚጠይቀው አዲስና ዲሞክራሲያዊ ጉዳናን ነው::

2. ከየካቲት እንቅስቃሴ ወዲህ የኤርትራ ጥያቄ አመጣጥ

ከየካቲት እንቅስቃሴ ጀምሮ እስከሰኔ 22 ድረስ የኤርትራ ግንባሮች አቋም 'ሁኔታው ወዴት እንደሚያመራ እናያለን' የሚል ነበር:: ምንም እንኳ አንዳንድ የጥቃት እርምጃዎች አልፎ አልፎ ቢወሰዱና አንዳንድ የሃይለስላሴ መንግስት ሹሞች በግንባሮቹ ተቀጊያቸ ቢገደሉም፡ ጠቅላላው የግንባሮቹ አቀራረብ የዛሬውን አይመስልም ነበር:: የአሁኑ የጦር ሃይሎች ደርግ በተፈጠረና አድሃሪያቸን በያዘ ማግስት፡ ሰኔ 24 ቀን አንድ የግንባሩ ወኪል ሱኔታ ለተባለው የጣሊያን ጋዜጣ በሰጠው መግለጫ እንደሚከተለው ተናግሮአል::—

> በኢትዮጵያ በመካሄድ ላይ የነበረውን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ በሚመለከተው በኩል 'ለኤርትራ ሕዝብ ትርጉም የሚኖረው ነገር የኢትዮጵያ መንግስት እስካሁን የነበረውን የመስፋፋት ፖሊሲ የለወጠ እንደሁ ነው:: ቁምነገረኛ ፖለቲካ ሊኖር የሚችለው የኤርትራ ትግል የታወቀ እንደሆነና ያለፉት 13 አመታት ትግል ለነፃነት መሆኑ የተረጋገጠ መሆኑን ነው፣ የዚህም መደምደሚያ የሰላም ውይይት መሆን አለበት:: እስከዚያ የኢትዮጵያን ሁኔታ በጥብቅ እንከታተላለን:: ጊዜያዊው ሁኔታ ከቀጠለና የጥንቱ ፖሊቲካም ከቀጠለ ኢትዮጵያ ማንም ሊቆጣጠረው ወደማይችል ካኦስ/ምስቅልቅል/ መጓዙ ነው::
>
> 'የኢትዮጵያ ወታደሮችና ሃቀኛ ብሄራዊ ሃይሎች መፍትሄ ማግኘት አለባቸው:: ....ኢኤልኤፍና ፒኤልኤፍ/ሁለቱ ግንባሮች/ በሁሉም በኩል፡ በመሳሪያም ጭምር፡ ድርጊቶቻቸውን...እንዲያስፋፉ እናደርጋለን:: በአውሮፓና በሌሎችም የአለም ክፍሎች ያሉት መልእክተኞቻችን ፕሮፓጋንዳቸውን አጠንክረው የአለምን ሕዝብ ድጋፍ ማስገኘት አለባቸው:: በሴፕቴምበር/መስከረም/ ጉዳያችን ከተባበሩት መንግስታት ፊት እንዲቀርብ ይደረጋል!:' /ሰርዘና ቅንፍ የተጨመረ/

ማንም ሊቆጣጠረው የማይችል 'ካኦስ'፡ ጠቅላላ ድብልቅልቅ፡ የሚለውን አስተሳሰብና የመሳሪያ ትግል ማስፋፋት የሚለውን በዚህ ሁኔታ ከማናቸውም ተራማጅ የማይጠበቀውን አባባል ወደጎን ብንተው፡ ከዚህ በላይ የጠቀስነው፡ ግንባሮቹ የሰላም ውይይት ይፈልጉ እንደነበር በግልጽ የሚያሳይ ይመስለናል:: ነገር ግን፡ በዚያኑ ሰሞን 'ኢትዮጵያ ትቅደም' የሚለውን መመሪያ ማስፋፋት የጀመረው የጦር ሃይሎች ደርግ በዚህ ጥሪ በመጠቀም ውይይቱ እንዲጀመር ለማድረግ ምንም እርምጃ አልወሰደም:: ይልቁንም 'ኢትዮጵያ ትቅደም'ን ከያዛቸው አላማዎች አንዱ 'የኢትዮጵያ አንድነት ፍፁምነት' መሆኑን በሰፊው በማብራራት 'ብሄረኛነትን'/ናሽናሊዝሙን/ ማጋነን ያዘ:: በተረፈም፡ ለሃይለስላሴ ካቀረባቸው የስልጣን መረከቢያ ድርድሮች አንዱ የፖለቲካ እስረኞች መለቀቅ መሆኑ ሲታወቅ፡ በንጉሡ 'ፈቃድ' የተባሉት እስረኞች ሲፈቱ፡ የኤርትራ እስረኞች ግን እንዳይለቀቁ አደረገ::

በግንባሮቹም በኩል ሆነ በደርጉ በኩል ይህውዥንብር የሞላበት ሁኔታ ከወር በላይ ቆይቶ ነሃሴ 10 ቀን ሃያ ሰስቱ የኤርትራ እንደራሴዎች የሃይለስላሴን ፓርላማ ትተው ወጡ:: ለዚህ እርምጃቸው የሚሰጡአቸው ምክንያቶች የመንግስቱን በኤርትራ ጉዳይ ቸልተኝነትና

የአስመራን አኮኖሚ መሞት፡የአምሃራን ፍልሰት፡የኤርትራን የፖለቲካ እስረኞች አለመለቀቅና በዚህም ሌዩነት መደረጉን ነበር፡፡ ነሃሴ 14 ቀን ሚካኤል እምሩ ከፓርላማው ፊት ቀርቦ በፍፁም ግድየለሽነት 'የኤርትራ ችግር ከሌሎቹ የኢትዮጵያ ችግሮች የተለየ አይደለም'ሲል፣ በበኩሉ·የአሜሪካኖቹ ሰው የሆነው በሳቸው ደምነህ የፖለቲካ እስረኞች መለቀቅ የተባለው 'በመሳሪያ ሃይል የንጉሰነገሰቱን መንግስት የሚቃወሙትን አይመለከተም'፣ ስለዚህም ኤርትራ የፖለቲካ እስረኞች አይለቀቁም አለ፡፡

ምንም እንኳን ቢደርጉ በኩል ፍፁም ይቅርታ የማይደረግለት ቸለተኝነት ቢታይም፡ሚካኤል በተናገረ ማግስት፡በካይሮ የሚገኘው የነንባሩ/የኢሊኢፍ/ ወኪል ውይይት ይከፈት የሚል መግለጫ ያወጣል፡፡በዚህ መግለጫ ውስጥ ግንባሩ ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር ለኤርትራ 'ሙሉ ብሄራዊ ነፃነት'ውይይት ለመክፈት ዝግጁ መሆኑን ያመለክታል፡፡ውይይቱ የሚከፈትበትን አገር ሁለቱ ወገኖች/የኤርትራ ግንባርና የኢትዮጵያ መንግስት/ ይመርጣሉ፡፡ይሁንናም ለውይይቱ መከፈት ግንባሩ የሚያቀርበው ድርድር የኤርትራ ግንባር የኤርትራ ሕዝብ ህጋዊና ለብቻው ወኪል መሆኑን የኢትዮጵያ መንግስት እንዲያውቅለት የሚል ነበር፡፡በተጨማሪም የተባበሩት መንግስታት በፍጥነት አንድ መርማሪ ኮሚሽን ወደኤርትራ ልከው ይህ ኮሚሽን የሕዝቡን የራሱን እድል የመወሰን መብት እንዲጠብቅለትና በተባበሩት መንግስታት፡በአፍሪካ አንድነት ድርጅትና በአረብ ሊግ ቁጥጥር ስር በኤርትራ ሬፈረንደም/የሕዝብ ፈቃድ ጥያቄ/ እንዲደረግ ይጠይቃል፡፡

ከአምስት ቀናት በሗላ፡ማህሙድ ሰይድ ኢድሪስ የተባለው የግንባሩ ወኪል ይህንኑ የመሰለ መግለጫ በቤይሩት ይሰጣል፡፡የሚያቀርበው ድርድር ያው ግንባሩ የሕዝብ ወኪል መሆኑ እንዲታወቅለት ነው፡፡ምርጫው የሚደረገው ያው ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ድርጅቶች ስር ይሆናል ይላል፡፡ይኸኛውን መግለጫ ይበልጥም የውይይት ግብዣ የሚያደርገው የሚከተለው አረፍተ ነገር ይገኝበታል፡፡'ለኤርትራ ድራማ፡ለብዙ መቶ መንደሮች መደምሰስና ለሰባ ሺህ ኤርትራውያን መበታተን ዋናው ሃላፊ ሃይለስላሴ ነው፡፡'

እንደእውነቱ ከሆነ በነበረው ሁኔታ ከዚህ የበለጠ የሰላም እጅ ለመዘርጋት እንደማይቻል ግልጽ ነው፡፡መቸም አስራ ሶስት አመታት ሙሉ ለብሄራዊ ነ፣ነት ሲታገል የቆየ እጀ ኤርትራ ግንባር ያለ ድርጅት ውይይትን ለመክፈት ከ'ሙሉ ነፃነት' ያነሰ ነገር ለውይይት መንደርደሪያ ማቅረብ አይቸለምና፡፡. በዚህ አይነቱ ሁኔታ እንደምንም ተከራክሮ ዋናው ነገር —የውይይት መከፈት— እንዲገኝ ለማድረግ ሲቻል፡ደርጉ ግን አማን አንዶምን ወደኤርትራ ልኮ እርሱ ሕዝቡን እንዲደልል መረጠ፡፡

በርግጥም፡የውጭ አገር ጋዜጦች እንዳመለከቱት ሁሉ፡ያሜሪካኖች ሰው ነበረ የሚባለው አማን አንዶም ለጥቂት ጊዜም ቢሆን የኤርትራን ሕዝብ ለማወናበድ ችሎ እንደነበር የተደረገለት የጋለ አቀባበል አሳይቶአል፡፡ከአስራ ሁለት ቀናት ጉብኝት በሗላ ጳጉሜ 1 ቀን ወደ አዲስ አበባ ሲመለስ ለኤርትራ ሕዝብ የሚከተሉትን ነገሮች ለማስፈፀም ቃል ገብቶአል፡፡ከአጽበት አመት በፊት በኤርትራ ላይ የተጫነው የአደጋ ጊዜ አዋጅ እንደሚነሳ፣ የኤርትራ ኤኮኖሚ እንዲንቀሳቀስ እንደሚደረግ፣ በአምሃራ የፍልሰት ወንጀል የፈፀሙት ፖሊሶችና ወታደሮች ለፍርድ እንደሚቀርቡ፣ ከአራት መቶ በላይ የሆኑት ኤርትራውያን የፖለቲካ እስረኞች እንደሚፈቱ፣ ኤርትራውያን ወደውጭ አገር ለመሄድ ሲፈልጉ ችግር እንደማይደርስባቸው፣ የተዘጉት የኤርትራ እንዱስትሪያች እንደሚከፈቱ ወዘተ. ቃል ገብቶ ነበር፡፡ይሁንናም አማን አንዶም ኤርትራ በቆየበት ጊዜ በተለይ የጎበኘው የመንግስቱን ሰራዊትና የፖሊስ ክፍሎች ከመሆኑም በላይ፣ ደጋግሞ 'የኢትዮጵያና የኤርትራ አንድነት ፍፁም ነው፡፡ኤርትራ የኢትዮጵያ አንድ ክፍል ናት' በማለት በይፋ ተናግሮአል፡፡በተረፈም፡ከላይ ከተጠቀሱት ተስፋያች አንዱም እንኳን ከስራ ላይ ለማዋል እርምጃ አልተወሰደም፡፡

በደርጉ በኩል፡ባንድ ወገን የበጎ ፈቃደኛነት ጉድለትና ቸልተኝነት፡በሌላ ወገን ደግሞ ሃይለስላሴንና ግብረአበሮቻቸውን ከስልጣን የማስወገዱ ተግባር መንዛዛት ጉዳዩን ሲያዘገየው፤ በኤርትራ ግንባሮች በኩል ደግሞ የአማን ጉብኝት ግራ አጋብቶአቸው ለጥቂት ጊዜ ፀጥ ያሉ ይመስሉ ነበር፡፡መስከረም 2 ቀን ንጉሡ ከስልጣን ተወገደ፡፡ የኤርትራ ግንባሮች በሌላ ራቸው ከእንግዲህ አንዳች የተጨበጠ ውሳኔ ይደረጋል ብለው ከጠበቁ በሃላ፡መስከረም 15 ቀን ኦስማን ሳላህ ሳቤ/የፒኤልኤፍ አፈጉባኤ/በቤይሩት የጋዜጠኞች ጉባኤ አድርጎ የውይይቱን አሳብ ከማስጠንቀቂያ ጋር አቀረበ፡፡ይህ መግለጫ ከዚህ በላይ ካየናቸው ይበልጥ ጠንከር ያለ ቢመስልም፤ ከነዚያኞቹ ይበልጥ ሰላምን ፈላጊ እንደነበር ግልጽ ነው፡፡የኦስማን መግለጫ ዋና ይዘቶች እንደሚከተሉት ናቸው፡፡

አንደኛ፤ የግንባሩና የኢትዮጵያ መንግስት ወኪሎች በተባበሩት መንግስታት ተጠባባቂነት ስርጭውይይት ይከፈት ይላል፡፡የሃይለስላሴ መውደቅ ለዚህ ውይይት መከፈት ጥሩ ሁኔታን እንደ ፈጠረ ያመለክታል፡፡ሁለተኛ፤ 'የኤርትራ ግንባር ከብሄራዊ ነፃነት ሌላ ማንኛውንም መፍትሄ አጥብቆ መቃወሙን ይገልፃል፤'ሆኖም 'የኢትዮጵያን የንግድና የባህር ጥቅሞችና እንደዚሁም የሁለቱን ወገኖች መከላከያና ፀጥታ በሚመለከተው በኩል አንዳንድ ነገሮችን ለመቀበል/ከንቡሮች ለማድረግ/ ዝግጁ ነን' ይላል፡፡ሶስተኛ፤ የኤርትራ ሪፐብሊክን ግቡ የሆነውን ብሄራዊ ነፃነትን እስካላገኘ ድረስ ትጥቁን እንደማይፈታ ኦስማን አመለከተ፡ኢትዮጵያ ካንገራገረች ግን 'ኢትዮጵያን ከቀይ ባህር ፈጽሞ ለማራቅ ትግላችንን እንደምናፋፍመው' እንዲታወቅ በማለት ይደመድማል፡፡

በዚህ መግለጫ ውስጥ፡ቁጥር 2 የቀረበው የኦስማን አሳብ ምንም ትችት የማያስፈልገው [illegible] ነገር ይመስለናል፡፡በዚህ መግለጫ ምክንያት እንደሆነ አይታወቅም፡በማግስቱ መስከረም 16 ቀን፡በሁለቱ የኤርትራ ግንባሮች መካከል፡በከረን አጠገብ ሃይለኛ ግጭት ተደረገ፡፡ ኢሳይያስ የተባለው መሪ ተገደለ የሚባል ወሬም ተሰራጨ፡፡በዚህ ሁኔታ፡ኤርትራውያን ተዋጊዎች እርስበርስ ሲገዳደሉ፡የሰሜኑ ክፍለጦር በግንባሮቹ ላይ ሃይለኛ ማስጠንቀቂያ አወጣ፡፡በመካከሉ፡በኢትዮጵያ መንግስት በኩል በኦስማን መግለጫ ላይ ምንም እርምጃ ሳይወሰድ ሲቀር፡ መስከረም 25 ቀን ሁለቱ ግንባሮች በአስመራ አጠገብ ስብሰባ አደረጉ፡፡ይህ ሁለት ቀን የቆየ ብዙ ሺህ ሰው የተገኘበት ስብሰባ ሁለቱን ግንባሮች ያስታረቀ ይመስላል፡፡

ከዚህን ቀን ጀምሮ በኤርትራ ያለው ሁኔታ የተባባሰ ይመስላል፡፡መስከረም 26 ቀን የግንባሮቹ የስብሰባ ጉዳይ እንዳለቀ፡አማን አንድም እንደገና ወደአስመራ ሄዶ በሬዲዮ የተነበበ ጥብቅ ማስፈራሪያ ሰጠ፡በመግለጫው ውስጥ አማን 'የጦር ሃይሎች ደርግ ደም እንዲፈስስ አይፈልግም፡፡ነገር ግን ሁኔታው ካስገደደው ማንኛውንም እርምጃ ከመውሰድ አይቆጠብም፡፡... ...ለኢትዮጵያ ደህንነት ሰራዊቱ አስፈላጊውን እርምጃ ሁሉ በመውሰድ ኢትዮጵያ ትቅደም የሚለውን መመሪያ ከስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡' ከዚህ በሃላ ሃይለኛ ማስጠንቀቂያ በመስጠት አማን እንዲህ በማለት፡—'ይህንን የተሰጣችሁን እድል ካልተጠቀማችሁበት በሃላ ይቆጫችሃል፤ ሰራዊቱ ጥብቅ እርምጃ መውሰዱ የማይቀር ነውና፡፡ሰላምን በኤርትራ ለማስፈንና በኤርትራና በኢትዮጵያ መካከል የኖረውን አንድነት ለመጠበቅ እድል ተሰጥቶአችሁአል፡፡...'

እንግዲህ በሁለቱም በኩል በዚህ ሁኔታ ዛቻና ማስጠንቀቂያ ከተወረወረ በሃላ፤ የኤርትራ ግንባሮችም አንዳች የርስበርስ ግንኙነት ካደረጉ በሃላ፤ በዚያም በዚህም በጥቅምት ወር ምንም ነገር ሳይነሳና ሳይሰማ ጊዜው አለፈ፡፡ግንባሮቹ በበኩላቸው የአረብ አገሮችን እርዳታ ለማግኘት በይበልጥ ሲፍጨረጨሩ፡የኢትዮጵያ መንግስት ደግሞ የበጎ ፈቃድ ጓደኞችን በየቦታው እየላከ የእነዚሁ የነፃነት ግንባሮች ደጋፊ አገሮች እርዳታቸውን እንዲያቆሙ ለማድረግ ሞከረ፡፡

በዚህ ሁኔታ ለአንድ ወር ያህል በሁለቱም በኩል ውስጥ ውስጡን የዲፕሎማቲክ ትግል እንደቀጠለ የህዳር 13 ቀን የአማንና የ59ኙ ሰዎች መረሸን ድርጊት ተፈፀመ:: ኢምፔሪያሊስቶችና በርካታው የሶስተኛው አለም መሪዎች በደርጉ ላይ ትልቅ የማውገዝና የመኮነን ዘመቻ ሲከፍቱ ገንባሮቹም ይህንኑ ማስተጋባት ቀጠሉ::

በህዳር ወር ከሁለቱም ወገኖች በኩል የጦርነት ዝግጅት ሲደረግ ቆየ:: የኤርትራ ገንባሮች በይፋ እንደተናገሩት ሁሉ በርከት ካሉ የአረብ አገሮች በብዙ ሚልዮን ብር የሚቆጠር የመሳሪያ እርዳታ ሲያገኙ ደርጉ ደግሞ በበኩሉ በኤርትራ የሚገኘውን ጦር በብዙ ሺህ ወታደር በማጠንከር ዝግጅቱን ቀጠለ:: ቀደም የኤርትራን ገንባር ከመደገፍ ይቆጠቡ የነበሩት እንደነ ሳውዲ አረቢያና ኩዌይት ያሉ አድሃሪ መንግስታት ገንባሮቹን እንደሚደግፉ በግልጽ አስታወቁ:: በታህሳስ 12 'የኢትዮጵያ ሶሻሊዝም' ከታወጀ ወዲህም ኢምፔሪያሊስት አገሮች በፕሮፓጋንዳ በኩል የገንባሮቹን ትግል በመደገፍ የኤርትራን ጉዳይ ከባንግላዴሽና ከፍልስጥኤም ጉዳይ ጋር አመሳስለው ያቀርቡ ጀመር::

በታህሳስ አጋማሽ ላይ በኤርትራ፡ከኢትዮጵያ መንግስትና ከገንባሮቹ አስራ አምስት ሺህ ተዋጊዎች፡በጠቅላላው ሰላሳ ሺህ ተዋጊዎች ፊትለፊት ተሰልፈው ነበር:: በዚህ ሁኔታ፡ ታህሳስ 16 ቀን ያንዱ ገንባር ዋና ፀሃፊ የሆነው ኦስማን ሳላህ ሳቤ እንደገና በቤይሩት የጋዜጠኞች ጉባኤ ያደርጋል:: በዚህ የጋዜጠኞች ጉባኤ ላይ ኦስማን የሚያቀርባቸው ዋና ዋና ነጥቦች እንደሚከተሉት ናቸው:: የኤርትራ ገንባር ከሽፍታ/ጌሪላ/ ጦርነት ወደፊት ለፊት ጦርነት መሸጋገሩ ነው:: የኤርትራን ገጠር በሙሉ ከቁጥጥሩ ስር ያደረገው የኤርትራ ሪቮሉሽን ከእንግዲህ ድርጊቶቹን ከገጠር ወደከተማ በማዛወር ከተሞችን ለመያዝ ይዘጋጃል:: የጦር ሃይሎች ደርግ እንደ ሃይለስላሴ መንግስት ሁሉ ኤርትራን በጉልበት ለመያዝ ሲል ከሃያ ሺህ በላይ የሚሆን ወታደር በኤርትራ አስፍርአል:: ይሁንና የኤርትራ ገንባሮች በቅርቡ ፀረ ታንክ መሳሪያዎችን፡መድፎችን፡ ያውሮፕላን መከላከያዎችን በብዛት በማግኘታቸው ሃይላቸው ከኢትዮጵያ ሰራዊት ያነሰ አይደለም:: የኢትዮጵያ መንግስት በአስመራ ከአራት መቶ ሰዎች በላይ ይዞ ማሰሩንና ብዙዎቹንም መግደሉን፣ እንደዚሁም በኢትዮጵያ ሰራዊት ውስጥ ያሉት ኤርትራውያን ከድተው ለገንባሮቹ መግባታቸውን ከተመለከተ በኋላ ኦስማን በሚከተሉት የምስጋና ቃላት ጉባኤውን ፈጸሞአለ:— 'የኤርትራ ገንባር እንደነሊቢያ፡ዴሞክራሲያዊ የመን፡ኢራቅ፡ሶርያና ሌሎችም የአረብ አገሮች ያሉትን፡ገንባሩን የደገፉትንና እንደወዳጅ የሚቀርቡትን ሁሉ ያመሰግናል::' ይህ የኦስማን የጋዜጠኞች ጉባኤ የጦርነት አዋጅ እንደነበረ ግልጽ ነው::

በዚህ ሁኔታ፡የጦር ሃይሎች ደርግ ታህሳስ 19 ቀን በሚካኤል አምሩ የሚመራ ቡድን ወደአስመራ ልኮ ወደአራት መቶ ከሚጠጉ ያገር ሽማግሌዎችና የሃይማኖት መሪዎች ጋር ውይይት በማድረግ እርቅ፡እንዲፈለግ ለማድረግ ሞከረ:: ከነዚህ የኤርትራ ሽማግሌዎች ውስጥ 38 ተመርጠው ከገንባሮቹ ጋር ግንኙነት በማድረግ ሰላማዊ መፍትሄ የሚገኝበትን መንገድ እንዲፈልጉ ተደረገ:: ይሁን እንጂ፡ምንም እንኳን ቀደም ብሎ መደረግ የነበረበት ቢሆንም ሙከራው ተገቢ ነበር:: ደርጉ በሽማግሌዎቹ አሳሳቢነት አንዳንድ የበጎ ፈቃድ እርምጃዎችን ቢወስድም አሁን በአስመራ ከተማና አካባቢ በመካሄድ ላይ ያለው ጦርነት እንደሚያሳየው ሁኔታው ከመባባስ አላቆመም::

እንግዲህ ካለፉት ጥቂት ወራት ጀምሮ የኤርትራ ሁኔታ አመጣጥ ይህ ሲሆንና በሁለቱም ወገኖች በኩል ጥፋቶች መኖራቸው በማያጠራጥር አኳሃን ሲታይ፡በደርጉ በኩል የተደረጉት ዋናዎቹ መሆናቸው ለማንም ግልጽ ይመስላል:: በነሃሴና በመስከረም፡በተለይ ሃይለስላሴ ከወደቀ ወዲያ፡ከኤርትራ ገንባሮች የቀረበውን የውይይት ሃሳብ ደርጉ በቶሎ መቀበል ነበረበት:: የገንባሩ 'ሙሉ ነፃነትን' መጠየቅ በኛ አስተያየት ምንም ያህል እንቅፋት መሆን አልነበረበትም:: አስራ ሶስት አመት ሙሉ የታገለ ገንባር ለመነሻ ያህል ከዚህ ያነሰ ነገርን በመጠየቅ ውይይት ለመክፈት የማይመቸው እንደነበረ ሲታወቅ፡ደርጉ በዚህ ነገር ቸልተኝነቱንና 'ፍፁም

አንድነት'በማለት አድሃሪ የጉልበተ መፍትሄ አሳቡን ከስራ ላይ ለማዋል መሞከር አይገባውነበር::በሌላ በኩል ደግሞ የኤርትራ ገንባሮች ከቀርብ ጊዜ ጀምሮ ኢምፔሪያሊስቶች በደርጉ ላይ የሚያደርጉትን ከባድ ተጽእኖና ፕሮፓጋንዳ በመመልከት:ከእነዚህና ከሌሎች አድሃሪ ሃይሎች ጋር በመተባበር:ምንም እንኳን ለጊዜው በፀረ ዲሞክራሲያዊነቱ የማያጠራጥር ቢሆንም:ወታደራዊውን ደርግ እንደዋና ጠላት መቁጠርና ለማጥፋት መሞከር ትክክል አይመስለንም:: የሁለቱ ወገኖች የፖለቲካ ጥፋቶች በሰላማዊው ሕዝብ ላይ ያደረሱአቸው ጉዳቶች የኤርትራንና የኢትዮጵያን ሕዝቦች ከመቀራረብ ላይ እንዳያደርሱ ከሚያሰጋበት ሁኔታ ላይ የመጣነው በዚህ አይነት ነው::

## 3. ከኢትዮጵያ ህብረተሰባዊነት መታወጅ ወዲህ የሃይሎች አሰላለፍ

መላው አለም:ኢምፔሪያሊስት አገሮችም ጭምር:ምናልባት ፍፁም አድሃሪ ከሆኑት አንዳንድ አገሮች በስተቀር:የየካቲትን የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሪቮሉሽናዊ እንቅስቃሴ ወደመጀመሪያው ገደማ በበጎ አይን ይመለከቱት እንደነበር የታወቀ ነገር ነው:: ሃይለስላሴ ከስልጣን ሲገለል አድሃሪ ሃይሎች የእንቅስቃሴውን አዝማሚያ መጥላትና አልፎ አልፎም ማንቋሸሽ ጀመሩ::የቀድሞዎቹ አድሃሪ ባለስልጣኖች መረሸንና የኢምፔሪያሊስቶች በደርጉ ውስጥ ያሉአቸው ሃይሎች ለጊዜው መዳከም የብዙውን የአለም ፀረሪቮሉሽናውያን የስድብና የቁጣ መአት ሲያስከትል፣ የታህሳስ 12ቱ 'የኢትዮጵያ ህብረተሰባዊነት'አዋጅ ፈጽሞ አበድ ውሻ አድርጉአቸዋል::መላው ኢምፔሪያሊስት አለም ከማንቋሸሽና ከተግሳጽ ወደቀጥታ·የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ተዛወረ:: ተራማጁ አለም ግን·በበኩሉ ከተቆጠበ አቋም ወደቀጥታም ሆነ ዘወርዋራ ድጋፍ አልፎአል::

የኢትዮጵያ ሕዝቦች አንደኛ ዋና ጠላት የሆነው የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም መጀመሪያ በእንዳለካቸው አማካይነት:ከዚያም በደርጉ ውስጥና አካባቢ በአማን አንደም በኩል ያደረጋቸው ፀረሕዝብ ሴራዎች ለጊዜው ስለከሸፉበት 'የእርዳታውን'አገጣጣ በመለወጥ የሃይለስላሴ ሞግዚት በነበረበት ጊዜ የፈጠራቸውን ቡችሎቹንና አድሃርያንን በድብቅ ማዘጋጀትና ማጠናከር ጀምሮአል:: በአሁኑ ጊዜ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በአንድ በኩል በቢሮክራሲው ውስጥ ባሉት ሰዎቹ — እንደነበላቸው ጀማነህና ተካልኝ ገዳሙ ባሉት— በሌላ በኩል እንደነሳውዲ አረቢያ ባሉት አድሃሪ መንግስታት አማካይነት እነመንገሻ ስዩምን:ነጋ ተገኝን:አሊ ሚራህን:በውጭ ያሉትን መሳፍንትና የቀድሞ ባለስልጣኖች በማደራጀትና በማስታጠቅ የየካቲትን እንቅስቃሴ ውጤቶች ለመደምሰስና አድሃሪ ሃይሎችን መልሶ ከስልጣን ላይ ለማስፈር በብዙ መንገዶች በመጣር ላይ ነው::በወታደራዊው መንግስት ላይ ልዩ ልዩ የኤኮኖሚ ተጽእኖ ለማድረግም እየሞከረ ነው:: ለምሳሌ የንግስት ዘውዲቱን ሆስፒታል እስካሁን ሲያካሂዱት የነበሩ የአሜሪካን ሚሲዮኖች በቅርቡ በሙሉ ለቅቀው እንደሚወጡ ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር አስታውቀዋል::ከልኡል መኮንንም ሆስፒታል ስዊሶች እርዳታቸውን እንደሚያቋርጡ ሰሞኑን አስታውቀዋል ይባላል::ያንኪ አሜሪካኖችም የዘንድሮን ቡና እንደማይገዙ 'በአማካሪያቻቸው'በኩል በሰፊው አስወርተዋል::*

የኤርትራ ጥያቄ በኢትዮጵያ ውስጥ በመካሄድ ላይ ካለው ሪቮሉሽናዊ እንቅስቃሴ ተነጥሎ ሊታይ አይቻልም:: የሃይለስላሴ መገለበጥ:የጥቂት ሙሳፍንትና መኳንንት መረሸንና 'የኢትዮጵያ ሶሻሊዝም'መታወጅ፣ ኢምፔሪያሊዝምና የመላው አለም አድሃሪያች ባንድ በኩል:ደርጉና የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ በሌላው በኩል እንዲሰለፉ በማድረግ ላይ ነው::ኢምፔሪያሊዝምና በተለይም በቀይ ባህር አካባቢ የሚገኙት አድሃሪ ሃይሎች በኤርትራ ጥያቄ በመጠቀም ባሁኑ ጊዜ

---

* አሁን ሰሞኑን የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ለኢትዮጵያ መንግስት/ለደርጉ/ መሳሪያ ለመስጠት እንደሚፈልግ ጠቁሞአል::ይህ አዲስ የመግቢያ ታክቲክ ሊሆን ስለሚችል በደርጉ ውስጥም ሆነ ውጭ ያሉ ተራማጆች አጥብቀው እንዲያስቡበት ያስፈልጋል::

የየካቲቱን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ውጤት ለማጨናገፍ በኢትዮጵያ ሕዝቦች ላይ ለመዝመት በመዘጋጀት ላይ ናቸው:: የኤርትራ የነፃነት ግንባሮች ይህንን ሁኔታ አጢነው በመመልከት፣ አርግጥ በአሁኑ ጊዜ ፀረኢምፔሪያሊስት ትግልም እናደርጋለን የሚሉ ከሆነ፣ በሰፊው የኤርትራ ሕዝብ ጥቅም ላይ በመመስረት ሰላማዊ መፍትሄውን መፈለግ እንጂ ወደዱም ጠሉም ከኢትዮጵያና ከኤርትራ ሕዝቦች እውነተኛ ጠላቶች ጋር የሚያሰልፋቸውን እርምጃ መውሰድ አይገባቸውም::

በአሁኑ ጊዜ የቀይ ባህር አካባቢና የኢትዮጵያም ውስጣዊ ሁኔታ እንደእውነቱ ከሆነ በጣም የተወሳሰበ ነው:: በኤርትራ ጥያቄ አማካይነት ኢምፔሪያሊዝም: በተለይም ዋናው ጠላታችን የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም: የኢትዮጵያን ሪቮሉሽናዊ እንቅስቃሴ ለማጨናገፍ ይጣጣራል:: በፕሮፓጋንዳ ደረጃ የኤርትራን ግንባሮች እንደሚደግፍ የጋዜጦቹና የሬዲዮኖቹ ኦፊሲዬል ያልሆኑ ዘመቻዎች ያሳያሉ:: ዛሬ በዚህ ደረጃ ከደገፈ ነገ ደግሞ በግልጽ በመሳሪያም ጭምር ለመደገፍ የማይነሳበት ምክንያት ያለ አይመስለንም:: እንዳጋጣሚ ሆኖ የያንኪ ኢምፔሪያሊዝም በአለም— አቀፍ ደረጃና በውስጥም በብዙ ችግሮች ተወጥሮ ባይያዝ ኖሮ የሳንቶደሚንጉን የመሰለ እርምጃ እስካሁን በኢትዮጵያ ላይ ሳይወስድ አይቀርም ነበር ብሎ ለመገመት ይቻላል:: ከዚህ ሌላ ግን ባሁኑ ወቅት ኢምፔሪያሊዝም ከውጭ ካሉት መሳፍንትና መኳንንት ጋር ሆኖ የነመንገሻ ስዩምን: የነአሊሚራህን: የብሩን ልጆች ፀረሕዝብ ሴራዎችና ድርጊቶች እንደሚያደራጅ ምንም ጥርጥር የለውም::

በአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምና በቀይ ባህር አካባቢ ባሉት አድሃሪ ሃይሎች: በነሳውዲ አረቢያ: በነኩዌይት ትብብር ለጊዜው በኤርትራ ጥያቄ አማካይነት ፀረኢትዮጵያ የሆነ ግንባር ተቋቁሞአል ለማለት እንችላለን:: በሌላ በኩል ግን: በገሃድ እንደገለፀው ሁሉ: የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም እነዚህን አገሮች —ነዳጅ ዘይት የሞላባቸውን የአረብ አገሮች— ለመውረር ዝግጅት በማድረግ ላይ እንደሆነ ከኪሲንጀርና ከፍርድ መግለጫና ማረጋገጫ ወዲህ ያደባባይ ምስጢር ነው:: በዚህ አይነት: መንገድ ከተከፈተለትና የብዙ ሚልዮን ብር ወጭም አድርጎ ከቀናው፣ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ኤርትራን ለአረብ አገሮችም ሆነ ለኤርትራ ጥቃት የጦር ሰፈር ሊያደርጋት ይችላል ማለት ነው:: ይህ አደጋ ስላለ የኤርትራ ሰፊ ሕዝብ በጥብቅ እንዲያስብበት ያስፈልጋል::

ለማጠቃለል ያህል: ያሁኑ የውስጥና የውጭ ሁኔታችን እንደዚህ ነው:— በኤርትራ ጥያቄ በማሳበብ ኢምፔሪያሊዝምና አድሃሪያኖቹ የቀይ ባህር አካባቢ ሃይሎች በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ላይ ለመዝመት አይመለሱም:: በኢትዮጵያ ላይ ሲባልም በአሁኑ ጊዜ አገሪቱን በሚያስተዳድረው ደርግና በሰፊው ሕዝብ ላይ ማለት ነው:: እነዚህ ፀረሕዝብ ሃይሎች የኤርትራን ሕዝቦች ከመቸውም ይበልጥ በኢትዮጵያ መንግስት ላይ በመቀስቀስ: ከውስጥ የተነሱትን ባላባታዊ ሃይሎች በገሃድም ሆነ በስውር በመደገፍ በማደራጀትና በማበራታት፣ ሌሎችንም በየቦታው ለመቀስቀስ በመሞከር፣ በመንግስቱ ቢሮክራሲ ውስጥ ባሉት ሰዎቻቸውና ምናልባትም በደርጉ በራሱ ውስጥ ባሉት የቀኝ ሰዎች አማካይነት በልዩ ልዩ ደረጃ ብዙ ሳቦታጅ በማከናወን አሁን በደርጉ ውስጥ ያሉትን ተራማጆች ለማዳከምና ለመገልበጥ ይፈልጋሉ:: በርሱ ቦታ በባላባቶች ርዝራዦችና በቢሮ ከበርቴው የሚመራ: የኢምፔሪያሊስቶች ቡችላ የሆነ መንግስት ፈጥረው የጭቆናና የብዝበዛ ቀንበራቸውን መልሰው በኢትዮጵያ ሕዝቦች ላይ ለመጫን ይጣጣራሉ:: /ይሁንናም ኢምፔሪያሊዝምና ባላባታዊ ስርአት ገና ስላልተደመሰሱ ሰፊው ሕዝብ አሁንም ምንም አለማግኘቱን አንዘነጋም::/ እንግዲህ በአሁኑ ሰአት: ወደዱም ጠሉም: የኤርትራ ግንባሮች የተሰለፉትና እርዳታም የሚቀበሉት ከነዚህ አድሃሪ ሃይሎች ነው::*

---

* ኦስማን ሳሌህ ሳቤ ከሳኡዲ አረቢያ መንግስት ብዙ የገንዘብ እርዳታ እንደሚያገኝ ማስታወቁን የጀርመን ድምጽ ሬዲዮ በየካቲት 3 ቀን 1967 ገለፀ::

## 4. የኤርትራ ጥያቄ ዘለቄ መፍትሄና የተራማጆች ጊዜያዊ ተግባር

"ጋራተኞች ከሰራተኛው መደብ ማህበሮች የተለየ ማህበር የላቸውም::"

"በአጠቃላይ ከወዝአደሩ የተለየ ጥቅም የላቸውም::"

"የወዝአደሩን ንቅናቄ ለራሳቸው የተለየ አላማ ሲሉ አያጉበጡትም::"

"ጋራተኞች ከቀሪት የሰራተኛው መደብ ማህበሮች የሚለዩት በሚከተሉት ብቻ ነው::—

1. የልዩ ልዩ አገሮች ወዝአደሮች በሚያካሂዱቸው የትግል እንቅስቃሴዎች: የብሄር ልዩነት ሳያደርጉ የጠቅላላውን ወዝአደር ጥቅም ይዘው በግንባር ቀደምነት ይሰለፋሉ::
2. የሰራተኛው መደብ ከከበርቴው ጋር በሚያደርገው ትግል በልዩ ልዩ ደረጃ ላይ:በማናቸውም ጊዜና ስፍራ:የጠቅላላውን ንቅናቄ ጥቅም ይጠብቃሉ::"

"እንግዲህ ጋራተኞች:ባንድ በኩል:በማናቸውም አገር ህብረተሰቡን ወደፊት የሚገፋን ቀሳቀሰው: የሰራተኛው መደብ ብሄራዊ ማህበራት ግንባር ቀደም ቆራጥ ታጋዮች ናቸው::በሌላ በኩል ደግሞ:ከሰፊው ወዝአደር ይልቅ እነርሱ የጠቅላላውን ወዝአደር ንቅናቄ የጉዞ መስመር:የሚያልፍባቸውን ልዩ ልዩ ሁኔታዎችና የመጨረሻ ግብ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ አጣርተው የመረዳትና የማወቅ ችሎታ አላቸው::"
ካርል ማርክስና ፍሬደሪክ ኤንግልስ:ዘ ኮሙኒስት ማኒፌስቶ::

"ለብሄሮች ጥያቄ መፍትሄ የአገሪትዋ ሙሉ በሙሉ ዲሞክራሲያዊ መሆን መሰረትና አስፈላጊ ነው::" ጄ.ስታሊን:ማርክሲዝም ኤንድ ዘ ናሽናል ኮዌስችን:ገጽ 74

የኢትዮጵያ ተራማጆች ደጋግመው እንደገለፁት ሁሉ የኤርትራን ሕዝቦች የራሳቸውን እድል የመወሰን መብት ያውቁላቸዋል::የኤርትራም ሆነ የሌሎቹ ብሄሮች ጥያቄዎች በትክክል ሊፈቱ የሚችሉት ይህ ዲሞክራሲያዊ መብት ሲታወቅና ከስራ ላይ ሲውል ነው::ብሄሮች የራሳቸውን የወደፊት እድል የመወሰን መብት አላቸው ማለት ማንም በግድ ቋንቋቸውን እንዲደመስስ፣ ባህሉቸውን እንዲያንቋሽሽ፣ ማንነታቸውን እንዲያጠፋባቸው መብት የለውም ማለት ነው፣ አንድ ብሄር በፈለገው መንገድ:በፌዴሬሽን ሆነ በአተኖሚ ወይንም በሙሉ አንድነት ከሌላ ብሄር ጋር ሊያያዝ መብት አለው ማለት ነው፣ የለም አልፈልግም ካለም የመገንጠልና የራሱን መንግስት የመመስረት መብቱ የተጠበቀ ነው ማለት ነው::

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብም ሆነ የኤርትራ ሰፊ ሕዝብ የሰፊ ግዛትን:በወንድማማችነትና በፍፁም እኩልነት በመፈቃቀድ አብሮ የመኖርን ጥቅም ያውቃል::ድር ቢያብር አንበሳ ያስር እንደሚባለው ህብረት:ሰብሰብ ብሎ በአንድነት እየሰሩ መኖር ለጠላት አይመችም፣ አያስጠቃም:: ሰፊ አገር ለንግድ ለኢንዱስትሪና ለጠቅላላ ብልጽግና ያመቻል::ይህንን ሃቅ የተጨቆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ሁሉ ያውቃሉ::ስለዚህም በአሁኑ ጊዜ ምናልባት:ምናልባት የኤርትራ ሕዝቦች በታላቅ ጭቆናና ግፍ:በነዚህ አስራ ሶስት አመታት በደረሰባቸው ጭፍጨፋ ተማርረው ለመገንጠል ይፈልጉ እንደሁ አናውቅም::መገንጠሉና የራሱን መንግስት ማቋቋሙ መሰረታዊ መብታቸው ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ ይህን እርምጃ መውሰዱ ለሰፊው የኤርትራ ሕዝብ ይጠቅማልና ይገነጠሉ አንልም::

ይሁንናም የብሄሮች ሁሉ:ትልቅም ሆነ ትንሽ:የራሳቸውን የወደፊት እድል የመወሰን መብት መታወቁና በትክክል ከስራ ላይ መዋል አለበት::ብሄሮች ቋንቋቸውንና ጠቃሚ የሆኑትን ባህሎቻቸውን በነፃ እንዲያዳብሩ መደረግ አለበት::ማንም ሰው በውስጥ አስተዳደራቸው ላይ ጣልቃ ተጽእኖ እንዳያደርግ መከልከል አለበት::ኢትዮጵያን ከብሄሮች እስር ቤትነት ወደብሄሮች ማበቢያ ስፍራ እንድትለወጥ ማድረግ ያስፈልጋል፣ ይቻላልም::ይህም የሚሆነው የሁሉም እኩልነት ከላይ በተጠቀሰው አይነት ከስራ ላይ ሲውል ሲሆን፣ እውነተኛ የሕዝቦች አንድነት

በሳንጃና በመድፍ ያልተቋቋመ አንድነት፡በማግባባትና በመፈቃቀር ላይ የተመሰረተ አንድነት ሊመሰረትና እንደአለት ፀንቶ ሊኖር የሚችለው በዚህ መንገድ ብቻ ነው።

እውነተኛ ሶሻሊስቶች በብሄሮች ጉዳይ ላይ የሚወስዱት አቋም ሁለት አንፃሮች አሉት። በአንድ በኩል ብሄሮች የራሳቸውን እድል በራሳቸው ለመወሰን ያላቸውን መብት ያለአንዳች ማወላወል የደግፋሉ። ይህም ማለት በመሰረቱ ማንኛውም ብሄር በመሰረቱ ከመረጠ፡ ያለምንም ተጽእኖ ከሌሎች ብሄሮች ጋር በፌዴሬሽን ወይም በአተኖሚ ወይንም በአንድነት መልክ መንግስት አቋቁሞ ሊተዳደር እንደሚችልና ካስፈለገም የራሱን ነፃ መንግስት ለማቋቋም ሙሉ መብት እንዳለው ያምናሉ ማለት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ እውነተኛ ሶሻሊስቶች የብሄሮችን ጉዳይ ከጠቅላላው የአካባቢው ጊዜያዊ ሁኔታ ጋር ጥብቅ የሆነ ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት እንዳለው ያምናሉ ማለት ነው ። ይህም ማለት አንድ ብሄር ከሌሎች ተነጥሎ የራሱን ነፃ መንግስት ለማቋቋም በሚጠይቅበት ጊዜ ይህንን ጥያቄ ደ[illegible]ፈ [illegible]ረንም ይቃወሙ እንደሆን ለመወሰን አስቀድመው ጠቅላላውን ጊዜያዊ የኅብረተሰብ ሁኔታ ያጠናሉ። የብሄሩ መገለጠል የተገንጣዩን ብሄርና የቀረትንም ብሄሮች ሰፊ ሕዝብ ፍላጉት ያሟላ እንደሆነ፤በሁለቱም በኩል ያሉትን ሰፊ ሕዝቦች ለዲሞክራሲና ለደህንነት የሚያደርጉትን ትግል ያራምድ እንደሆነ መገንጠሉን ያለማወላወል ይደግፉታል ። ነገር ግን የብሄሩ መገንጠል ከጊዜያዊው ኅብረተሰባዊ ሁኔታ ጋር ሲመሳከር ከሰፊው ሕዝብ ጥቅምና ፍላጉት ጋር የሚፃረር፤ሰፊው ሕዝብ ለዲሞክራሲና ለደህንነት የሚያደርገውን ትግል የሚያዳክም ሆኖ ካገኙት መገንጠሉን ይቃወማሉ። ያም ሆነ ይህ በመሰረቱ እውነተኛ ሶሻሊስቶች በመሰረቱ የብሄሮች ጉዳይ በሰላማዊና በዲሞክራሲያዊ መንገድ፡ የሰፊው ሕዝብ ፈቃድ በግልጽ ታውቆ መወሰን እንዳለበት ያምናሉ።

በማንኛውም ብሄር የመገንጠል ጥያቄ ላይ አቋም ሲወስዱ ከነዚህ መሰረተሃሳቦች ዝንፍ ከተባለ ውጤቱ ወይ የኔ ብሄር ከሁሉ ብሄሮች በላይ ነው የሚሉትን ትምክህተኛ ብሄረኞችን/ሾቪኒስቶችን/ አለበለዚያም፡ የኔ ብሄር ከሁሉም ብሄር ለዩነቱን በግድም ሁነ በውድ ጠብቆ መኖር አለበት በማለት የልዩ ልዩ ብሄሮችን ሰፊ ሕዝቦች መቀራረብ የሚቃወሙ ጠባብ ብሄረኞችን የሚደግፍ ይሆናል። ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት መሰረተሃሳቦች ላይ በመመርኮዝ የኤርትራን ፕሮብሌም ለመፍታት የሚቀጥሉትን ሃሳቦች እንሰነዝራለን፡—

ከሁሉ አስቀድሞ ይህ የሰፊው ሕዝብ ደም መፍሰሻ የሆነው የወንድማማች ጦርነት በፍጥነት እንዲቆምና የሰፊው ሕዝብ መጉሳሳት እንዲቀር፤ ሁለቱም ወገኖች —ግንባሮቹና የኢትዮጵያ መንግስት— ሌላውን ወገን በቅድሚያ ምንም አይነት ግዴታ እንዲገባ ሳይጠይቁ፡ሳይውሉ ሳያድሩ ለሰላም ውይይት ተቀምጠው በአንዳንድ የመነሻ ስምምነቶች ላይ ለመድረስ ግዴታ እንዳለባቸው አውቀው መቀበል ይኖርባቸዋል።

ሁለተኛ፡ የኤርትራ ተገንጥሎ መውጣት ወይንም ከኢትዮጵያ ጋር በአንድ አይነት የፖለቲካ ግንኙነት ተያይዞ የመኖር ጉዳይ ከመወሰኑ በፊት የኤርትራ ሰፊ ሕዝብ ስለወደፊት እድሉ አስላስሎና ተወያይቶ በዲሞክራሲያዊ መንገድ ያለምንም ተጽእኖ ለመወሰን የሚችልበት ሰላማዊ ሁኔታ ተፈጥሮ ለተወሰነ ጊዜ እንዲቆይ ያስፈልጋል። የጊዜው እርዝመት በሁለቱ ወገኖች መካከል በስምምነት መወሰን አለበት። እዚህ ላይ መታወስ የሚገባው ግን ሰፊው የኤርትራ ሕዝብ ድርድሩን ከመጀመሩ በፊት ጉዳዩን ለማብላላትና በትክክል ለማየት በቂ ጊዜ እንደሚያስፈልገው ነው። በዚህ በሰላም ጊዜ ውስጥ በኤርትራም በኢትዮጵያም ሙሉ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ተረጋግጠው፡ሰፊው ሕዝብ በሁለቱም በኩል ሰፋ ያለ ውይይት ሊያደርግበት ይገባል።

ሶስተኛ፡ ይህ በእርቅ በስምምነት የሚወሰነው የሰላምና የውይይት ጊዜ እንዳለቀ የኤርትራ ሰፊ ሕዝብ ያለምንም ተጽእኖ በዲሞክራሲያዊ መንገድ ድምጽ በመስጠት የወደፊት እድሉን በምን አኳሃን ለመወሰን እንዳሰበ ፍላጉቱን ገልጾ፤ ይህም ፍላጉት ያለአንዳች ማወላወል በስራ ላይ እንዲውል መደረግ አለበት።

ነገር ግን ይህ በሚሆንበት ጊዜ መታየት ያለባቸው:—

1. ወታደራዊው መንግስት ፀረኢምፔሪያሊስትና ፀረፊውዳል መሆኑን በተግባር ጭምር ቢገልጥም የሰፊውን ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ መብቶችና ነፃነቶች እንደከለከለ ነው::በኢኮኖሚ በኩል የወሰዳቸው እርምጃዎች —ዋና ዋናዎቹን የማምረቻና የማከፋፈያ ድርጅቶች:መሰረታዊ የሃብት ምንጮች የሕዝብና በሙንግስት በመንግስት ቁጥጥር ስር ማድረግ የሶሻሊዝምን ፈለግ የተከተለ በመሆኑ የሰፊውን ሕዝብ ጥቅም የሚያረካ ቢሆንም:ሰፊውን ሕዝብ በመንግስት ስልጣን ውስጥ እንዳይካፈል አግልሎታል::ደርጉ ሶሻሊዝምን ያውጅ እንጂ አሁንም ብዙ ፀረሶሻሊስት የሆኑ ድርጊቶች ይፈጽማል::እነዚህን ሙሉ በሙሉ እስከአላስወገደ ድረስ አቋሙ ሙሉ በሙሉ ሊደገፍ አይችልም::

2. የኤርትራ ነፃ አውጭ ግንባሮች ለኤርትራ ሰፊ ሕዝብ ምንድነው የሚያቀርቡለት.እንደሚታወቀው የኤርትራ ልዩ ልዩ ግንባሮች የተለያዩ ኘሮግራሞች አሉአቸው::ለማቋቋም የሚፈልጉት መንግስት የትኛውን ኘሮግራም ይከተላል፣ የማንንስ ጥቅም ይጠብቃል. የሰፊው ሕዝብ መንግስት ከሆነ የግድ ፀረኢምፔሪያሊስትና ፀረፊውዳል መሆን ይኖርበታል፣ ይህ አርግጥ ነው. በመሰረቱ ኤርትራ ራስዋ የብዙ ብሄሮች አገር ናት::የኤርትራ ልዩ ልዩ ብሄሮች እድላቸውን ለመወሰን ያላቸውን መብት ግንባሮቹ ያውቁላቸዋልን. በነዚህና በሌሎችም ተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን አቋም አጥርተው ለሰፊው ሕዝብ መግለጽ ይኖርባቸዋል::

በኤርትራ ጥያቄ,ላይ ያለን አቋም ይህ ሲሆን አሁን ደግሞ የተራማጆችን ጊዜያዊ ተግባር በማውሳት እንደምደም::

ከዚህ በላይ ያቀረብነው ትንተና እንደሚያሳየው ሁሉ:የኢትዮጵያ ሪቮሉሽን በአሁኑ ጊዜ ከትልቅ አደጋ ላይ አለ ብለን እንገምታለን::ያመንግስትን ስልጣን የያዘው የጦር ሃይሎች. ደርግ ፀረኢምፔሪያሊስትና ፀረፊውዳል እርምጃዎችን —ከፀረዲሞክራሲያዊ እርምጃዎች ጋር ቢቀላቅልም— እልፍ እልፍ ስለወሰደ በአሁኑ ጊዜ ከሰፊው ሕዝብ ጉን ተሰልፍ ይገኛል::በዚህም ምክንያት በርሱና በኢትዮጵያ ሕዝቦች ጥንዱ ጠላቶች:በኢምፔሪያሊዝምና በፊውዳሊዝም:መካከል ቅራኔ አለ::ስለዚህምበአሁኑ ሰአት:ከዚህ በላይ እንደተባለው:እነርሱ በደርጉ ውስጥና በውጭም ያሉትን ተራማጆች ለማስገለበጥና የሰፊውን ሕዝብ እንቅስቃሴ ለማጨናገፍ ብሙዝመት ላይ ይገኛሉ::በማንኛውም መንገድ የኢትዮጵያ ተራማጆች ከነዚህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቶች ጋር እንዳይሰለፉ ትልቅ ጥንቃቄ መደረግ አለበት እንላለን::በአሁኑ ሰአት ደርጉ በፀረዲሞክራሲያዊነቱ ከሰፊው ሕዝብ ጋር ቅራኔ ቢኖረውም በደርጉ ተራማጆችና በኢምፔሪያሊዝም—ፊውዳሊዝም መካከል ያለው ቅራኔ እጅግ በጣም የላቀ መሆኑ የማያጠራጥር ነው::

ከዚህ በላይ እንዳመለከትነውና ገሃዱ ያገሪትዋ ሁኔታ እንደሚያሳየው ከእንግዲህ በኢትዮጵያ ሲቪል ጦርነት ተጀምሮአል ብለን እንገምታለን::ባንዱ በኩል የተሰለፉት ኢምፔሪያሊዝምና የባላባታዊው ስርአት የቀድሞ ቀንዳሞች እንመንገሻ ስዩም:እነመስፍን ና መርእድ ብሩ:እነነጋ ተገኝ:አሊሚራህ ወዘተ. ያሉት አድሃሪያዎች ናቸው::በተጨማሪም የኢምፔሪያሊዝም ቡችሎች በደርጉና በመንግስቱ ቢሮክራሲ ውስጥ ተገጥግጠው ሲመቻቸው የተቻላቸውን ሁሉ ሳቦታጅ በማድረግ ከነዚያ ጋር ይሰለፋሉ::ወደፊት ወታደራዊው መንግስት ያውጃል የተባለው የመሬት ይዞታ አዋጅ ሲታወጅ ደግሞ የገጠሩ ባላባትና ነፍጠኛ ሁሉ ገበሬውን እራሱን አወናብዶ ለማስነሳት መሞከሩ የማይቀር ነው::በሌላ በኩል ግን የተሰለፉት ለጊዜው በደርጉ ውስጥና ውጭ ያሉት ተራማጆችና ሰፊው ሕዝብ ናቸው ለማለት የሚቻል ይመስለናል::በደርጉ ውስጥ ያሉት ተራማጆች ሁኔታውን ደህና አድርገው ባለመረዳታቸው ተራማጁ ወገን በሚገባ ተደራጅቶ አፈርገፊውን ገበሬና ወዝአደሩን እንዲያደራጅ አልተደረገም::እንግዲህ በአኛ ግምት የተጀመረው ወይንም በመጀመር ላይ ያለው የሲቪል ጦርነት ለሰፊው ሕዝብ በሚያመች ሁኔታ ነው ለማለት ያዳግታል::

በዚህ ሁኔታ የእኛ የተራማጆች ተግባር በተቻለ ፍጥነት መደራጀትና ማደራጀት ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም::ከኢምፔሪያሊዝምና ከአድሃሪ ሃይሎች ጋር በሚደረገው ትግል ከደርጉ ተራማጆች ጋር በንተባበርም ለዲሞክራሲ የምናደርገውን ትግል መቀጠል አለብን፣ ዲሞክራሲያዊ መብቶችና ነፃነቶች ስራ ላይ እንዲውሉ፣ ሰፊው ሕዝብ የራሱ በሆነው መንግስት ስልጣን ውስጥ እንዲሳተፍ፣ የብሄሮች ጥያቄና በተለይም የኤርትራ ችግር ሊፈታ የሚችለው፡የታገደው ሶሻሊዝም ራሱ ስር ለመያዝና ለመለምለም የተሻለ እድል ሊኖረው የሚችለው በዲሞክራሲ ውስጥ መሆኑን በማብራራትና በማስረዳት ትግሉን መቀጠል ያስፈልገናል::

በኛ ግምት የኢትዮጵያ ሪቮሉሽናዊ ጉዳና ጠመዝማዛና ዐጣገባ የቀሰበት ይሆናል::እንዳንዱ መንገዱ የሚጠመዘዘበት ማእዘን ላይ ታይ ይችላል::አንዳንዴም በቀላሉ ለገወናበዶባችው የምንችለባቸው ሁኔታዎች ሊፈጠሩ ይችላሉ::ይሁንናም የኢትዮጵያ ተራማጆች ከደገማቱም ከተጠበቁና መንገዳችውን ሁሉ በሰይንሳዊ መንገዱ-ብየደረሻው ከቀየሱ የሚጠበቅባቸውን አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ ይችላሉ ብለን እንገምታለን::

ይሁንናም:ስለደርጉ ፀረዲሞክራሲያዊ ድርጊቶችስ ምን እናድርግ? የደርጉ ፀረዲሞክራሲያዊ እዋጆች፡የደርጉ ተራማጆችን በእስር ቤት ከአድሃሪያኑ እኩል ማጉርስ የመደራጀትና የማደራጀት ስራችንን አያደናቅፍም ወይ? በርግጥ የደርጉ ፀረዲሞክራሲያዊ አስተሳሰቦችና ድርጊቶች የሕዝቡን ትግል ወደሗላ ይጎትቱታል::ደርጉ ምንም እንኳን አገርወዳድ ቢሆንም እስካሁን በወበዳችው አንዳንድ ስህተተኛ እርምጃዎች የሕዝቡን ትግል ወደኋላ እንደጎተተ ምንም አይጠረጠርም::እነዚህንና የመሳሰሉትን የደርጉን ፀረዲሞክራሲያዊ ውሳኔዎችና እርጃዎች ማጋለጥ አለብን::ከደርጉ ጋር በዚህ ደረጃ የፖሊቲካ ትግል ማድረግ ይኖርብናል ማለት ነው::

እንደራጅ፣ እናደራጅ::

QUOTATION

" The economic, political and cultural conditions of a given nation constitute the only key to the question how a particular nation ought to arrange its life and what forms its future constitution ought to take. It is possible that a specific solution of the question will be required for each nation If the dialectical approach for a question is required anywhere it is required here, in the natinal question."

J. Stalin: Marxism and The Natinal Question. P. 26.

" To repeat: the concrete historical conditions as the starting point , and the dialectical presentation of the question as the only correct way of presenting it and is the key to the national question ."

ibid.p. 32

" The principle of nationality is historically inevtable in bourgeois society and taking this society into due account, the Marxist fully recognises the historical legitimacy of national movements. But to prevent this recognition from becoming an apologia of nationalism, it must be strictly limited to what is progressive in such movements, in order that this recognition may not lead to bourgeois ideology obscuring proletarian consciousness.

V.I. Lenin, Coll. Works,

Vol.20, p. 34, Moscow 1964.

" The communists do not form a separate party opposed to the working class parties.

"They have no interests separate and apart from those of the proletariat as a whole.

" They do not set up any sectarian principles of their own by which to shape and mould the proletariat movement.

" The communists are distinguished from the other working class parties by this only: 1. IN the national struggles of the proletarians of the different countrie they point out and bring to the front the common interests of the entire proletariat, independently of all nationality; 2. In the various stages of development which the struggle of the working class against the bourgeoisie has to pass through, they always and everywhere represent the interest of the movement as a whole.

" The communists, therefore, are on the one hand, practically, the most advanced and resolute section of the working class parties of ever country, that section which pushes forward all others; on the other hand, theoretically, they have over the great mass of the proletariat the advantage of clearly understanding the line of march, the conditions, and the untimate general results of the proletarian movement."

K. Marx and F. Engels.
The Communist Manifesto.

" Thus the compete democrtization of the country is the basis and condtion for the solution of the national question ."

J. Stalin: Marxism and the National Question . P.74.